# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 102 ሚያዝያ 21 2002 ዓ.ም

**ምርጫን እንደመሰለያ መሳሪያ የሚጠቀመው ወያኔ በድህረ ምርጫ 97 በህዝባችን ላይ የፈጸመው አይነት ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ እንዳይደገም ከተፈለገ፣ ነጻ እና ገለልተኛ የሆነ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት፤ ለሁሉም እኩል የሚያገለግል የሚዲያ አገልግሎት፤ ታማኝነታቸው ለህገመንግሥቱ ብቻ የሆነና ከፖለቲካ ወገናዊነት የጸዱ የፖሊስ፤ የመከላኪያና የደህንነት ተቋማት መመስረት ይኖርበታል።**

**ለወያኔ እድሜ መራዘሚያ ህጋዊና ሞራላዊ መሰረት እንዲያስገኝ ታስቦ በሚካሄድ ምርጫ መሳተፍ ለህዝባችን የሚያስገኘው ፋይዳ አይኖርም!!!**

## ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በአውሮጳ ምክር ቤት በተካሄደ ስብሰባ ላይ ተገኝተው ንግግር አደረጉ

የግንቦት 7 ንቅናቄ ሊቀመንበር የሆኖት ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፥ "የአፍሪቃ ቀንድ ፈተናዎች" በሚል ርእስ በአካባቢው በሚታዩት አሳሳቢ የፖለቲካ ችግሮች ላይ ግንዛቤ ለማስያዝ በአውሮጳ ምክር ቤት በተዘጋጀ ስብሰባ ላይ ከትናንት በስቲያ በመገኘት ንግግር አድርገዋል።

በብራሰልስ ቤልጂየም በክብርት አና ጎሜዝ መሪነት በተካሄደው በዚሁ ስብሰባ ላይ፣ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ባደረጉት ንግግር የመጪው የግንቦት ወር ምርጫ ውጤት አስቀድሞ የታወቀ ብቻ ሳይሆን በአገሪቱ ነፃ ምርጫን ለማድረግ አመቺ ሁኔታ የለም ብለዋል። ይህንንም ለማስረዳት ወያኔ ከምርጫ 97 በኋላ የወሰዳቸውን እርምጃዎች የዘረዘሩ ሲሆን፤ ከነዚህም ውስጥ አዲስ የወጡት አፋኝ ህጎች፣ የሰብአዊ መብት ረገጣዎች፣ የብርቱካን ሚደቅሳ እና ሌሎች ንጹሃን ዜጎች እስር፣ እንዲሁም የሚዲያ ተቋማት በአገዛዙ ፍጹም ቁጥጥር ስር መዋል ይገኙበታል።

በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ ይህ ሆኖ ሳለ የአውሮፓ ህብረት በጉዳዩ ላይ ያለው አቋም ያሳዘናቸው መሆኑን ገልጸው ህብረቱ እየተከተለ ያለውን ፖሊሲ እንደገና ሊመረምር ይገባዋል ብለዋል። ይሁን እንጂ፥ ኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲን በአገራቸው እውን ለማድረግ የውጭን ሃይል እገዛ መጠበቅ እንደማይገባቸው ዶ/ር ብርሃኑ ገልጸዋል። **(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**

## በካናዳ አገር ቶርንቶ ከተማ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ወያኔ የጠራውን ስብሰባ በመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ ወጡ

ከተለያዩ ድርጅቶችና ማህበራት የተሰባሰቡ ኢትዮጵያውያን በመተባበር ወያኔ ጠርቶት የነበረውን ስብሰባ በመቃወም ሰልፍ እንደወጡ አንድነት ለሰብአዊ መብትና ዴሞክራሲ የሚባለው ድርጅት ማክሰኞ እለት ለዝግጅት ክፍላችን በላከው መግለጫ ገልጿል።

ይኸው ስብሰባ የተዘጋጀው የኢንቨስትመንት ፈቃድ እና መሬት እንደሚሰጣቸው ቃል ለተገባላቸው ጥቂት ምርጥ ሰዎች እንደሆነ የታወቀ ሲሆን፤ ስብሰባው ግን ከታቀደለት አጀንዳ ወጥቶ ወያኔ በኢትዮጵያ እየተካሄደ ነው ወደሚለው ዴሞክራሲያዊ ሂደት በመለወጡ አንዳንዶቹ ተሳታፊዎች ቁጣቸውን መግለጻቸውን መግለጫው አሳይቷል።

ስብሰባው ከሚደረግበት ህንጻ ፊት ለፊት የዘረኛውን የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ወንጀሎች የሚያሳዩ መፈክሮች ይዘው ሰልፍ የወጡት ኢትዮጵያውያን አንድነት ለሰብአዊ መብት እና ለዴሞክራሲ በተባለው **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ አሁንም እርዳታን ለፖለቲካ ፍጆታ ማዋል መቀጠሉን አዲስ መረጃዎች አሳይተዋል

ከሃያ አምስት አመታት በፊት ጀምሮ እርዳታን ለፖለቲካና ለግል ጥቅም ማዋሉ በበርካታ አካላት የተረጋገጠበት ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ አሁንም በህገ-ወጥ ተግባሩ እንደቀጠለበት መሆኑ ታወቀ።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የወባ በሽታን ለመከላከል በእርዳታ ያገኛቸውን የወባ ትንኝ መከላከያ አጎበሮች ባደባባይ ለአገዛዙ ካድሬዎች፣ ለዘመዶቻቸውና በመጪው ምርጫም ወያኔን ሳይወዱ በግድ ለመምረጥ ቃላቸውን ለሰጡ ግለሰቦች እያደለ መሆኑን የደረሰን ዜና አሳውቋል።

መረጃዎቻችን እንደሚያሳዩት፥ በወባ በተጠቁ አካባቢዎች የሚኖሩት ሰዎች፣ እነዚህን አጎበሮች ያለምንም አድሎ መቀበል ሲገባቸው፤ "ወያኔን እንመርጣለን" በሚል ጽሁፍ ላይ ፈርመው ቃል እንዲገቡ እየተገደዱ ነው። የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ያናገራቸው አንዳንድ ግለሰቦች ቃል ለመግባት ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተው የትንኝ መከላከያ ሳይቀበሉ የቀሩ ሲሆን፤ ፈርመው የተቀበሉትም ያንን ያደረጉት እርዳታውን ለመቀበል ሲሉ ብቻ መሆኑን ገልጸውለታል።

ኢትዮጵያ ውስጥ እርዳታ ወይም የመንግስት አገልግሎቶችን ላለማጣት ሲባል ለወያኔ የሃሰት ድጋፍ መስጠት እየተለመደ መሄዱን በተለያዩ ጊዜያት ከግንቦት 7 ድምጽ እና ከሌሎች ምንጮች የወጡ ዘገባዎች ማሳየታቸው ይታወሳል። ሂውማን ራይትስ ዋች የተባለው አለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ተከራካሪ ድርጅት በቅርቡ ላወጣው ሪፖርት ቃሉን የሰጠ አንድ **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

ግዜ — ግንቦት 7 ዜና

## ለኢትዮጵያ የሚሰጠው የውጭ እርዳታ የገዢውን ፓርቲ የአፈና ምህዳር ለማስፋፋት እየዋለ መሆኑ መጋለጡን ቀጥሏል

ሄለን ኤፕስቴን የተባሉ የጤና ጥበቃ ተመራማሪ፥ የኢትዮጵያን የጤና ጥበቃ እስትራተጂ ለማጥናት በአገሪቱ ውስጥ ቆይታዎችን ካደረጉ በኋላ በቅርቡ ባወጡት ሪፖርት፤ ከውጭ የሚመጣው እርዳታ የገዢውን ፓርቲ የአፈና እና የቁጥጥር ምህዳር ለማስፋፋት ከመዋሉ ባሻገር የዜጎችን ህይወት እየለወጠ እንዳልሆነ ገልጸዋል።

ተመራማሪዋ ወደተለያዩ የገጠር ቀበሌዎች ተጉዘው ለም እና አረንጓዴ በሆነ አካባቢ የተራቡ ሰዎችን ማየታቸው እንደገረማቸው ገልጸው፤ ለዚህ ረሃብ መከሰት በአገዛዙ እና አገዛዙን በሚፈሩ ለጋሽ ቡድኖች የሚሰጡት እንደ ድርቅና የአፈር መሸርሸር ያሉ ምክንያቶች አጥጋቢ ሆነው እንዳላገኟቸው ገልጸዋል። የችግሩ መሰረት በገበሬዎቹ ላይ የሚደረገው ቁጥጥር እና የሰብአዊ መብት ረገጣ ነው ብለዋል።

ወያኔ ጫካ እያለ ጀምሮ እርዳታን ለፖለቲካ ጥቅም እንደሚያውል በሰፊው የተዘገበ ሲሆን፤ በኢትዮጵያውያን ስም ከለጋሾች የሚገኘው እርዳታ በጨመረ ቁጥርም የችግረኞቹን ዜጎች ኑሮ ከማሻሻል ይልቅ ወያኔ በዜጎች ላይ የሚያደርገውን ቁጥጥር እንዲያጠብቅ እንደሚረዳው ይነገራል።

## የኦሮሞ ፌዴራሊስት ኮንግረስ ፓርቲ አባል የሆኑ ግለሰብ በወያኔ አባላት በደረሰባቸው ድብደባ መሞታቸው ታወቀ

የኦሮሞ ፌዴራሊስት ኮንግረስ ፓርቲ አባል የሆኑ ኢትዮጵያዊ ዜጋ በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ሃይሎች በጠብመንጃ ሰደፍ ተደብድበው ለሞት መብቃታቸውን ሮይተርስ የዜና አገልግሎት የፓርቲውን አመራር በመጥቀስ ዘግቧል።

አቶ ቢያንሳ ዳባ የተባሉት ግለሰብ መጋቢት 29 ቀን 2002 አመተ ምህረት፥ ወደ መኖሪያ ቤታቸው መጥተው አባል ለሆኑበት ፓርቲ ሰዎችን መመልመሉን እንዲያቆሙ ባዘዟቸው የገዢው ፓርቲ አባላት በጠብመንጃ ሰደፍ መደብደባቸውን የኦሮሞ ፌዴራሊስት ኮንግረስ ፓርቲ መሪ አቶ ቡልቻ ደመቅሳ ለሮይተርስ ዘጋቢ ተናግረዋል። አቶ ቢያንሳ በደረሰባቸው አደጋ ምክንያት ሆስፒታል ገብተው ከቆዩ በኋላም ሚያዚያ 8 ቀን 2002 አመተ ምህረት ህይወታቸው ማለፉን አቶ ቡልቻ ገልጸዋል።

ከዚሁ ፓርቲ ጋር መድረክ የተባለው የተቃዋሚ ፓርቲዎች ስብስብ አባል የሆነው አረና ትግራይ ፓርቲም ከጥቂት ሳምንታት በፊት አንድ እጩውን በግድያ ማጣቱ ይታወሳል። አቶ አረጋዊ በርሄ የተባሉት ኢትዮጵያዊ ዜጋ በሚያስተዳድሩት ሆቴል ቤት ውስጥ ጨለማን ከለላ አድርገው በመጡ ግለሰቦች አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ መገደላቸው በሰፊው ተዘግቧል። ከአቶ አረጋዊ ግድያ በኋላም በጅማ ዞን የአንድነት ፓርቲ አባል የሆኑ ዜጋ አራት ጊዜ በጩቤ መወጋታቸው ይታወሳል።

ዘረኛው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ስልጣን ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ በአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶች እና ሌሎች አማካኝነት የሚወጡ ሪፖርቶች በኢትዮጵያ ውስጥ በየአመቱ የሚፈጸሙ ህገ-ወጥ ግድያዎችን፣ ድብደባዎችንና እስራቶችን እንደሚዘረዝሩ ይታወቃል።

## አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ፤ ኢትዮጵያውያን ከእሰጣ ገባ የፖለቲካ ጭቅጭቅ እንዲቆጠቡ ጥሪ አቀረቡ

የግንቦት 7 የነፃነት፣ የፍትህና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ከፍተኛ አመራርና ዋና ጸሃፊ የሆኑት አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ እሁድ፣ ሚያዝያ 17 ቀን 2002 ዓም የኢትዮጵያ ወቅታዊ ጉዳዮች ውይይት መድረክ በመባል ለሚታወቀው ማህበር በሰጡት ቃለ-መጠይቅ ኢትዮጵያዊያን ገንቢ ካልሆኑ አተካራዎች በመቆጠብ በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ እንዲያተኩሩ ጥሪ አቅርበዋል።

የኢትዮጵያችን ዋናና አንገብጋቢ የፖለቲካ መፍትሄዎች የሚመነጩት ህዝብን የስልጣን ባለቤት ከማድረግ ተቀዳሚ ተግባር መሆኑ ምንጊዜም መዘንጋት የለበትም ያሉት አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ፤ ከምርጫ 97 በተገኘው ልምድ ወያኔ በምንም አይነት ሁኔታ ስልጣንን በሰላማዊ ምርጫ የመልቀቅ ፍላጎት የሌለው ዕብሪተኛና ጎጠኛ ሃይል ስለሆነ፤ በተባበረና በተቀናጀ ህዝባዊ ትግል አሽቀንጥሮ በመጣል ወደፊት ለምንም አይነት አምባገነንነት እድል ሊከፍት የማይችል አስተማማኝ መሰረት ላይ ሊቆም የሚችል የነጻ ተቋማት ምስረታ ትግል የሁላችንም ቅድሚያ ሊሆን ይገባዋል ብለዋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመድረክ አመራር ውስጥ ባሉ አንዳንድ ግለሰቦች የቀድሞ ታሪክ ዙሪያ በአገር ቤትና ከአገር ውጭ እየተደረገ ያለው ክርክር ሊኖረው ስለሚችለው ፋይዳ የተጠየቁት አቶ አንዳርጋቸው፤ በኢትዮጵያ እውነተኛና ዘላቂ የሆነ አዎንታዊ ለውጥ እንዲመጣ የሚፈልጉ ዜጎች ሁሉ **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## ከወጣት ቢያንሳ ዳባ ጋዲሳ መስዋትነት ስለ ሁለገብ ትግል የምንማረው ቁም ነገር

ሰላማዊ ታጋይ የወጣት ቢያንሳ ዳባ ጋዲሳን ሞት የሰማነው በሃዘን ነው። በትግራይ በአቶ አረጋዊ ገብረዮሃንስ መገደል ምክንያት ከደረሰብን ሃዘን ሳናገግም አሁን ደግሞ በኦሮሚያ ክልል ተመሳሳይ ግፍ ተፈጽሟል። ቢያንሳ ረዥም ህልም የነበረው የ23 ዓመት ወጣት ተማሪ ነበር። ይህ ወጣት በሰላማዊ መንገድ ለውጥ ማምጣት ይቻላል ብሎ በማመኑ መድረክ እንዲመረጥ ሲቀሰቅስ ነበር። የወያኔ ተላላኪ የኦህዴድ ካድሬዎች ከድርጊቱ እንዲቆጠብ ማስጠንቀቂያ ቢሰጡትም ወጣቱ ግን ያመነበትን መከወን ቀጠለ። በመጨረሻም አቶ ቢያንሳ ዳባ ጋዲሳ ከፉኛ ተደብድቦ ሕይወቱ በሆስፒታል ውስጥ ማረፉ ተሰማ። የዓለም ታዋቂ የዜና አውታሮች ይህንኑ ዘገቡ።

ልማደኛቹ ውሸታሞች በረከት ስምዖንና ሽመልስ ከማል ግን "ግለሰቡ ታሞ እንጂ ተደብድቦ አልሞተም። እንዲያውም የእኛ አባል ነበር፤ ከፈለጋችሁም ማስረጃ እናሳያችሁ በማለት" አስደናቂ ክርክር ከፍተዋል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በወጣት ቢያንሳ ዳባ ጋዲሳ ሞት የተሰማውን ጥልቅ ሃዘን እና ለከፈለው መስዋዕትነት ያለውን ክብር እየገለፀ ለቤተሰቦቹ መጽናናትን ይመኛል።

የዘንድሮ ምርጫ መንግሥታዊ ሽብርን ከድምፅ ዘረፋ ማስቀደሙ ልዩ ባህርዩ ሆኗል። ወያኔ ከምርጫ 97 ተምሬዓለሁ የሚለው ሽብርን ከምርጫው የማስቀደም አስፈላጊነት መሆኑ በተግባር እያየነው ነው።

ይህም ሆኖ ግን የበረከትና ሺመልስ መግለጫ ተጨማሪ ትኩረት የሚያሻ ሆኖ አግኝተነዋል። ሁለቱም መዋሸት ልማዳቸውም ሥራቸውም በመሆኑ ነገ ምን እንደሚሉ ባናውቅም እስካሁን ያልካዷቸውን ሁለት ጉዳዮችን መነሻ እናድርግ።

1. አቶ ቢያንሳ ዳባ ጋዲሳ በድብደባም ይሁን በበሽታ ሕይወቱ አልፏል፤
2. አቶ ቢያንሳ ዳባ ጋዲሳ የመድረክ አባል ለሆነው አፍዴን ሲቀሰቅስ ነበር።

በረከትና ሺመልስ "አቶ ብያንሳ አባላችን ነው" ያሉት እውነት ከሆነ ምንን ያመለክታል?

የበረከትና ሺመልስ ጭንቅላቶች መሥራት ጨርሶ አቁመው ካልሆነ በስተቀር የሚናገሩት እውነት ከሆነ በመዝገባቸው ያሰፈሯቸው ሰዎች በሙሉ የምር አባሎቻቸው እንዳልሆኑ ማሳያ በሆናቸው ነበር። እንዲያውም "በወይን ለመኖር" የተሰበሰቡ "አባሎች" አጋጣሚው ሲመቻች ብቻ ሳይሆን አንዳንዶቹ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሁነው እንኳን እያለ ፊት ለፊት ወያኔን ሊጋፈጡት እንደሚነሱ ማረጋገጫ ሊሆነው በተገባ ነበር። ለበረከትና ሺመልስ ግን አንድ ሰው የወያኔ አባል ነው ማለት ወያኔን ይደግፋል፤ ተቃዋሚ ደግሞ ይጠላል ማለት ነው። ይህ ድምዳሜ እውነት ነውን?

ለመሆኑ ሲዳማ ውስጥ ያሉት አባላቸው ለሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ስለሰጡት ምስክርነት ሰምተው ይሆን? እንዲህ ነበር ያሉት፡-

*እኔ የኢህአዴግ አባል ነኝ፤ ግን የምደግፈው ተቃማሚዎችን ነው። የኢህአዴግ አባል መሆን ማለት ምንም ማለት አይደለም። የኢህአዴግ አባል የሆንኩት እርዳታ ስለምፈልግ ነው። .... ርዳታ ለማግኘት ደረሰኝ - የኢህአዴግ መዋጮ ከፋይ አባል መሆኔ ማረጋገጫ ያስፈልገኛል። መጨቆንና መረሳት ስለማልፈልግ እከፍላለሁ።*

የሰብዓዊ መብት ተሟጋቹ ዓለም ዓቀፉ ድርጅት "አንድ መቶ የመጨቆኛ ስልቶች" በሚል ርዕስ ባወጣው የጥናት ሪፖርት እንዳብራራው በመላ ሃገሪቱ - ከጫፍ እስከ ጫፍ - የሚሰማው እሮሮ ተመሳሳይ ከመሆንም በላይ አንድ ዓይነት ነው።

ግንቦት 7 ከዚህ በፊትም በዚህ ጉዳይ ላይ ባወጣው ርዕሰ አንቀጽ እንደገለፀው ሥራ ለመቀጠር፣ የደረጃ እድገት ለማግኘት፣ ለእርዳታ፣ ለማዳበሪያ ግዢ፣ የምክር አገልግሎት ለማግኘት፣ ለትምህርት እድል ወይም ለሌላ ማናቸውም ጥቅም አሊያም ከዘወትር ጭቅጨቃ ለመገላገል ተብሎ የወያኔ አባልነት ፎርም መሙላት የራስን ክብር አሳልፎ መስጠት ነው። ትላልቅ የጥቅም ድለላዎች እና ማስፈራሪያዎችን ተቋቁመው "እንቢኝ ያሉ" ኢትዮጵያዊያን በመኖራቸው እንኮራለን። ሆኖም ግን "ፎርም መሙላት እኮ ምንም ማለት አይደለም" እያሉ እራሳቸውንም ሌላውንም የሚያሞኙ ወገኖችም የሚጀግኑበት አጋጣሚ እንዳለ ደግሞ እንገነዘባለን። ይህ ለበረከትና መለስ አይታያቸውም። እነሱን የሚያስደስታቸው የቁጥራ መብዛትና ዜናችን በእርስ በርስ ስለላ ማቆላለፋቸው ነው።

አቶ ቢያንሳ ዳባ ጋዲሳ የወያኔ አባል የአባልነት ፎርም ይሙላም አይሙላም በመሰለው መንገድ ወያኔን ሲታገል ሕይወቱን ሰውቷልና የሰማዕትነት ክብሩ አይቀነስም። እንዲያውም የበረከትና ሺመልስ ወሬ እውነት ከሆነ ለጊዜዓዊ ጥቅም ሲሉ አልያም በፍርሃት ምክንያት የወያኔ የአባልነት ፎርም የሞሉ ወገኖቻችንን የሚያደፋፍር አኩሪ ተግባር ሆኖ አግኝተነዋል።

ከአቶ ቢያንሳ ዳባ ጋዲሳ መስዋዕትነት የምንቀስመው ትምህርት የወያኔ አባልነት ፎርም ይሙሉም አይሙሉም "እንቢ ለወያኔ" ያሉ ወገኖቻችን የሕዝብን ከበሬታ የሚያገኙ መሆኑን ነው። ሁላችንም የምንመዘነው በሥራችን እንጂ የአንድ ወይም የሌላ ድርጅት አባል በመሆን ወይም አለመሆናችን አይደለም።

የተቃማዊ ፓርቲ አባል መሆን ብቻውንም ለክብር አያበቃም። የወያኔ አባልም ሆነው እያለ የወያኔን እድሜ ለማሳጠር የሚተጉ መኖራቸውን እናውቃለን። ሁለገብ ትግል ስንል ይኸንንም ይጨምራል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## ከኢትዮጵያ ተባረው የነበሩ ኤርትራዊያን ንብረቶች የሆኑ ቤቶች በወያኔ ካድሬዎች በህገ-ወጥ አራጣ ተሸጠው እንደነበር ታወቀ

በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት ከኢትዮጵያ ተባረው የነበሩ የኢትዮጵያ ወይም የኤርትራ ዜግነት የነበራቸው በርካታ ኤርትራውያን ንብረቶች በወያኔ ካድሬዎች በህገ-ወጥ አራጣ ተሸጠው እንደነበር የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ለማወቅ ችሏል።

በወቅቱ የኤርትራውያኑን ቤቶች ከወያኔ ካድሬዎች ህገ-ወጥ በሆነ አኳኋን ገዝተው የነበሩት ግለሰቦችም፣ በቅርቡ የወያኔው አገዛዝ ለፖለቲካ ፍጆታ ሲል ኤርትራውያን ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው ንብረቶቻቸውን እንዲወስዱ ጥሪ ማድረጉን ተከትሎ መጠበባቸውን ለማወቅ ተችሏል። ቤቶቹን የገዙበት ሁኔታ ህጋዊ ስላልሆነና ባለቤትነታቸውን የሚደግፍ ህጋዊ ዶኩመንት ባለመኖሩ፣ እራሳቸውን ከችግር ውስጥ ለማውጣት በሚል ቤቶቹን በርካሽ መሸጥ መጀመራቸውን ዘጋቢያችን ከተለያዩ ምንጮች ያገኛቸው መረጃዎች አስረድተዋል።

ዘረኛው እና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ስልጣን በጥቂት ምርጦች ቁጥጥር ስር ለማድረግ በቀረጸው ፖሊሲ አማካኝነት፤ ስልጣን ላይ በቆየባቸው ባለፉት ሃያ አመታት ዘርፈ-ብዙ ዘረፋዎችን ሲያካሂድ መቆየቱን የሚያሳዩ በርካታ ዘገባዎች ከዚህ ቀደም ማውጣታችን ይታወቃል።

## ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በአውሮጳ ምክር . . . ከገጽ 1 የዞረ

ከገጽ 1 የዞረ

በዚሁ ስብሰባ ላይ የኖርዌዩ ተመራማሪ ሚ/ር ሲግፍሬድ ፓወስሽንግ፣ የምርጫው ውጤት አስቀድሞ የተወሰነ ስለመሆኑ ተስማምተው፤ የአውሮፓ ህብረት የሚልከው የምርጫ ታዛቢ ቡድን መሄዱ ካልቀረ ግን አባላቱ በኢትዮጵያ ያለውን እውነተኛ የፖለቲካ ሁኔታ ለመረዳት ከአዲስ አበባ ውጪ ወዳሉ የገጠር አካባቢዎች መሄድ አለባቸው ብለዋል።

ክብርት አና ጎሜዝ በበኩላቸው የወያኔ አገዛዝ ለሚያደርገው አፈና ጠንካራ ወቀሳ ካደረጉ በኋላ፤ ዘረኛው መለስ ዜናዊ በአፍሪካ ዋነኛው አምባገነን እንደሆነና በማንኛውም መንገድ መወገድ እንዳለበት ተናግረዋል።

## በትግራይ ክልል በአዲ ዳይሮ ከተማ የተከሰተ ፍንዳታ አምስት ሰዎችን ገድሎ ከ20 በላይ ማቁሰሉ ተዘገበ

ቅዳሜ፣ ሚያዝያ 16፣ 2002 አመተ ምህረት በትግራይ ክልል አዲ ዳይሮ ከተማ ቡና ቤት ውስጥ በደረሰ ፍንዳታ አምስት ሰዎች ሞተው ከሃያ በላይ መቁሰላቸውን ሬውተርስ የዜና አገልግሎት ዘግቧል።

ፍንዳታው በተከሰተበት ቀን በሰአታት ውስጥ የወጣው የሬውተርስ ዘገባ የትግራይ ክልል ፕሬዚደንት የሆነው ጻጋይ በርሄን ጨምሮ የክልሉ አስተዳዳሪዎች እንደተለመደው ለወንጀሉ የኤርትራ መንግስት ተጠያቂ ነው ማለታቸውን ዘግቧል። ኢትዮጵያ ውስጥ ፍንዳታ በደረሰ ቁጥር የወያኔው አገዛዝ በፍጥነት የኤርትራን መንግስት ወይም በትጥቅ ትግል ውስጥ ያሉ ድርጅቶችን እንደሚወነጅል ያስታወሱ አንድ አስተያየት ሰጪ፤ በዚህ አኳኋን ፍትህ የሚነፈጉት ንጹሃን ዜጎች እንደሚያሳዝኗቸው ለግንቦት 7 ድምጽ ሬድዮ ጋዜጠኛ በላኩት የኢ-ሜይል መልክት ገልጸዋል።

ለግንቦት 7 ድምጽ ራድዮ ከዚህ ቀደም ቃለ-መጠይቅ የሰጡ አንድ የወያኔ ፖሊስ ወንጀል መርማሪ መኮንን ፤ በተደጋጋሚ በአዲስ አበባ ውስጥ ደርሶ የነበረውን ፍንዳታ ወያኔ እራሱ ካቀነባበረ በኋላ በአነጣ አባልነት የሚጠረጠራቸውን የኦሮሞ ተወላጆች አስር ከራሱ የመሳሪያ ግምጃቤት ያወጣውን መሣሪያ እያሸከመ በተሌቪዥን ካሜራ ቀራጮች ፎቶ እያስነሳ ውንጀላውን ለህዝብ ያቀርብ እንደነበረ መግለጻቸው ይታወሳል። ከግንቦት97 ወዲህ ተቃውሞዎችን ለማዳከም ባደረገው የተቀናጀ ዘመቻ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ጊዜያዊ ድል ያገኘ የመሰለው ወያኔ፤ የራሴ ምሽግ ነው ብሎ ይኩራራበት በነበረው ትግራይ ውስጥ ያልጠበቀው ህዝባዊ ማዕበል ስለተነሳበት ህዝቡን ለማሸበርና ለማስፈራራት የተቃዋሚ ፓርቲ አባል ከመግደል ጀምሮ ቀደም ሲል በአዲስ አበባ ከተማ ያደርግ እንደነበረው አሁን ደግሞ ፈንጅ እያስቀበረ በማስፈንዳት ወንጀል ለመከላከል በሚል ሰበብ ከምርጫው በፊት ተጨማሪ የፌደራል ፖሊሲ ሃይል በቦታው ለማስፈር እቅድ እንዳለው ከውስጥ አዋቂ ምንጮቻችን የተገኘው መረጃ ያመለክታል። ይህንን እራሱ ያቀነባበረውን ፍንዳታ በኤርትራ ላይ ማሳበብ የተፈለገውም የትግራይን ህዝብ "ጠላትህ መጣብህ" በማለት ስሜቱን ወደራሳቸው ለመመለስ እንደሆነ እነዚሁ ምንጮቻችን አክለው ገልጸዋል።



የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

ሃይለ ሀሳብ

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 102 ሚያዝያ 21 2002 ዓ.ም፤ ገጽ.3

# ወደፊት መራመድ እንዴት አቃተን? ለወደፊቱስ ምን ማድረግ እንችላለን?

ዶ/ር ታደሰ ብሩ (ማርች 27 ቀን 2010 አስሎ፣ ኖርዌይ በተካሄደ ህዝባዊ ስብሰባ ላይ ያቀረቡት ጽሁፍ) **ክፍል 3 (የመጨረሻ ክፍል)**

ክቡራትና ክቡራን ወደ ዋነኛው ጥያቄዬ ልመልሳችሁ። ለምንድነው ወደፊት መራመድ ያልቻልነው?

1. እንደ ፈታሹ ትናንሽ ምልክቶችን በጥንቃቄ ተከታትለው ሊመጣ የሚችለውን እድልም ሆነ አደጋ የሚያመላክቱን በቂ ልባም ሰዎችን አላፈራንም። የነበሩን ጥቂቶችም አልተሰሙም። የኃይለሥላሴ መንግሥት አደጋ ላይ መሆኑ በርካታ ምልክቶች ነበሩ። ብዙ ባይሆኑም ጥቂት ምሁራን ምልክቶቹን አንብበው ደፍረው መክረዋቸዋል፤ አልሰሟቸውም። የሳቸው አለመስማት በራሳቸውና በቤተሰቦቻቸው ላይ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ላይ ያደረሰውን ኪሳራ የምናውቀው ነው። የመንግሥቱም መንግሥት የውድቀት ምልክቶች እጥረት አልነበረበትም። አሁንም ጥቂት ብልህና ደፋሮች ምልክቶቹን አንብበው ለመምከር ሞከሩ፤ አልሰማቸውም። የመንግሥቱ ድንቁርና መለስ ላይ ጣለን። የመለስ መንግሥት የውድቀት ምልክቶች መታየት ከጀመሩ ቆይቷል። ጥቂቶችም ቢሆኑም ምልክቶቹን አንብበው ምክር ለመለገስ የጣሩ ነበሩ፤ አሉምም። መለስ ግን ምክሮችን ከመስማት መካሪዎቹን መግደል ይቀለዋል። ከመለስ በኋላ ምንድነው የሚመጣው? እስካሁን እኛ ራሳችን እድሎችን ልንፈጥር ይቅርና የተፈጠሩ እድሎችን እንኳን መጠቀም አልቻልንም። እንደ ማኅበረሰብ የልባሞች እጥረት አለብን። ያሉንን ጥቂት ልባሞችን ያለመስማት ደግሞ ተጨማሪ ችግር አለብን።
2. እንደ ፈጣኑ ፈጣን ተግባራዊ እርምጃዎችን መውሰድ አለመቻላችን ወደፊት መራመድ ላለመቻላችን ሌላው ምክንያት ነው ብዬ አምናለሁ። እርምጃዎቻችን በጣም ዘገምተኞች ናቸው። ማኅበረሰባችን በኤጭ ዓይነት ሰዎች የተሞላ ነው። ኤጭና አሃ ግድግዳ በማፍረስ እንደደከሙት ሁሉ እኛም ጉልበታችን ፋይዳ በሌላቸው ጉዳዮች ላይ እየጨረስን ፋይዳ ላላቸው ጉዳዮች የሚሆን አቅም እናጣለን። እንደ ኤጭና አሃ በማይረቡ ጉዳዮች በመነታረክ ተጠምደን በዙሪያችን ምን እየሆነ እንዳለ ማስተዋል ያቃተን ይመስለኛል። ለምሳሌ ጥቂት በማይባሉ ወገኖቻችን ጭንቅላት ውስጥ ያለችው ኢትዮጵያ ድሮ የነበረችው ኢትዮጵያ እንደሆነች እገምታለሁ። እውነት ለመናገር ያቺ ኢትዮጵያ ዛሬ የለችም። በራሳችን ዳተኝነት ኢትዮጵያችን ዘላቂ ጉዳቶች ደርሰውባታል። ይህንን መካድና የድሮዋ ኢትዮጵያ እንድትመጣ ማንጎራጎርም ሆነ ማቅራራት ዋጋ የለውም። ከቀድሞይቷ በብዙ እጥፍ የምትሻል ፍትህ፣ ነፃነትና ዲሞክራሲ የሰፈነባት አዲስ ኢትዮጵያን ፈልገን ማግኘት ሲገባን በድሮዋ ኢትዮጵያ ላይ መቆዘማችንን ቀጥለናል።
3. በትረካው ውስጥ አሃ አስቀድሞ የማሰብም ሆነ ፈጣን እርምጃዎችን የመውሰድ ችሎታ ያልታደለ ነው። እነዚህን ድክመቶች ያካካሱት በርካታ ነገሮች አሉ። ከእነዚህም ዋነኛው ግልጽ ራዕይ የነበረው መሆኑን ነው - ሁሌም አዲስ አይብ እንደሚያኝ ብሩህ ተስፋ ነበረው። እኛ ግን የራዕይም ችግር አለብን። በጭንቅላቱ ቤት መሥራት ያልቻለ መሬት ላይ ቤት ይሠራል ማለት ዘበት ነው። የምንፈልጋትን ውብ ኢትዮጵያ ምን እንደምትመስል ካላወቅን እሷን ለማግኘት እንደምን ዋጋ ልንከፍል እንፈቅዳለን? የብቁ መሪ ዋነኛው መለያ የጠራ ራዕይ ማፍለቅና ወደ ሌሎች ማስተላለፍ መቻሉ ነው። መሪ ከራዕዩ ሌላ የሚሰጠው ነገር የለውም። የምንናፍቃትና የምንወዳት ኢትዮጵያችን ምን እንደምትመስል የተረዳንበት መጠን እሷን የማግኘት እድላችንን ይወስናል። መድረሻውን የሚያውቅ መሰናክሎችን ዘሎም ሆነ ዞሮ መንገዱን ይቀጥላል። መድረሻውን የማያውቅ ግን የመጀመሪያው ብርቱ መሰናክል የጉዞው መጨረሻ ይመስለዋል። ለዚህም ነው "በአዕምሮህ መድረሻህን አስቀምጠህ ጀምር" (Start with an end in mind) የሚባለው።
4. ለውጥ አዲስ ራዕይን፤ አዲስ ራዕይ ደግሞ አዲስ አስተሳሰብን ይጠይቃል። አዲስ ራዕይን ለማሳካት አዳዲስ ስልቶች ያስፈልጋሉ። ያለፉት ሶስት ሥርዓት የተለያዩ ቢመስሉም ሲሰሩት የነበረው ሥራ ተመሳሳይ ነው። ወደፊት ላለመራመዳችን አንዱ ምክንያት አንድን ነገር ደገግመን እየሠራን የተለየ ውጤት ስንጠብቅ በመቆየታችን ነው። ይህ አሳዛኝ ክስተት የታየው በመንግሥታቱ ብቻ አይደም። ፓለቲካ ፓርቲዎቻችንም የሲቪክ ማኅበራትም የዚህ ሰለባዎች ናቸው። አንዳንድ ፓርቲዎች ከተቋቋሙ አርባ ዓመታት ቢሞላቸውም በአስተሳሰብ፣ በተግባርና ውጤት አንፃር ዛሬም ሲፈጠሩ እንደነበሩ ናቸው።
5. ፍርሃት ትልቁ በሽታችን ሆኗል። ይህ በአንፃራዊ መልክ የቅርብ ጊዜ ክስተት ቢሆንም እንደ ክፉ ወረርሽኝ በአጭር ጊዜ አጥቅቶናል። ትንታግ ይባል የነበረው ትውልድ በጉልምስናው ፈሪ መሆኑ ሳያንስፍርሃትን ለልጆቹ ማስተማሩ የሚያሳዝን ነው። ፍርሃት ተፈጥሮዓዊ ነው፤ ጠቃሚ ጎኖችም አሉት። ሲበዛ ግን ሽባ ያደርጋል። የአንዳንዶቻቸን የፍርሃት መጠን መግለጽ ያሳፍራል። ምስላችን ቢታይ፣ ድምፃችን ቢሰማስ፣ ኢሜላችን .... እንዲህ ተፈርቶ እንደምን ለውጥ ማምጣት ይቻላል? ከፍርሃት መውጫ አንዱ መንገድ እየፈሩም ቢሆን ማድረግ ነው። Do it scary ይባላል። የፈራነውን ነገር ማድረግ ስንጀምር ፍርሃታችን የተጋነነ እንደነበር እንረዳለን። በትረካው ውስጥ ይህ በጥሩ ሁኔታ ተገልጿል። እየተፈራም ቢሆን ዉሃ ውስጥ ካልተገባ ግን ዋናን መልመድ አይቻልም። አንዴ ዋና ከለመዳችሁ በኋላ በድሮ ፍርሃታችሁ ትስቃላችሁ። ሌላውም ነገር እንደዚሁ ነው።
6. ከውድቀቶች መማር አለመቻል። እንደ አሃ ላለው ብልህ ውድቀት ተስፋ ሰጪ ነገር ነው። ጣቢያ ቁጥር 5 ባዶ መሆኑን እንደውድቀት አላየውም እንዲያውም በግልባጩ ተስፋውን አለመለመለት። በአለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ አንብቤ ካስደሰቱኝ መፃህፍት አንዱ Failing Forward ወደፊት መውደቅ ይሰኛል። ወደፊት መውደቅ ከማዝገም እጅግ ..... እጅግ ... እጅግ ይሻላል። ከማይረባ ስኬት ደግሞ ዋጋ ላለው ጉዳይ ታልሞ ያልተሳካ ሙከራ በእጅጉ ይሻላል። ይህን ርዕስ ምናልባት ወደፊት እመለስበታለሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።
7. በመጨረሻ ላነሳው የምፈልገው አቢይ መልዕክት ለውጥ የሚጀምረው ከራስ መሆኑን ነው። እኛ አገር ብዙ ሰው ሌላ ሰው ታግሎ ለውጥን እንዲያመጣለት የሚፈልግ መሆኑ ባለንበት እንድረግጥ ካደረጉን ነገሮች አንዱ ብዬ አምናለሁ። ይህን አስተሳሰብ ሳንቀይር ለወደፊቱም ብዙ እንጓዛለን ብዬ አላምንም። ውጤት ቢገኝም ባይገኝም የለውጡ አካል መሆን ብቻውን የሚፈጥርልን ደስታ መኖር አለበት። ለሙብቱ በመታገል ላይ ያለ ሰው ጥቃት እንኳን ቢደርስበት ጥቃቱን የትግሉ አካል ስለሚያደርገው የግል ህመሙ አይሰማውም። ለውጥ እዚህ ደረጃ የደረሱ ተዋናይ ያስፈልጓታል። እኛ እንደህ አይነቱ የለውጥ ሃዋሪያት ከፍተኛ እጥረት አለብን።

**ክቡራትና ክቡራን**

በንግግሬ ያልተዳሰሰ፤ ባቀረብኩት ትረካም የተዘለለ አቢይ ነጥብ አለ። እሱ በለውጥ ሂደት ውስጥ የተቋማት ሚና ምንድነው የሚለው ነጥብ ነው። ይህ ቁልፍ ጥያቄ ነው። በለውጥ ሂደት ውስጥ የተቋማት በተለይም የፓለቲካ ማኅበራት ሚና ምን መሆን ይኖርበታል በሚለው ጥያቄ ላይ ያለኝን ሃሳብ በቅርቡ በሚደረግ ሌላ ስብሰባ ላይ ለማቅረብ እሞክራሉ።

የዛሬን ንግግሬን ላጠቃልል። ወደፊት መራመድ ለምን አቃተን? በእኔ እምነት ለዚህ ሰባት ዋና ዋና ምክንያቶች አሉ:: 1ኛ/ ማስተዋል አንሶናል። የነበሩንን ጥቂት አስተዋዮችን አልሰማንም፤ ዛሬም እየሰማናቸው አይደለም። 2ኛ/ ዳተኞች ነኝ። ትንንሽ ምቾቶችን እንኳን ማጣት አንፈቅድም 3ኛ/ ግልጽ የሆነ ራዕይ የለንም። መድረሻችንን አናውቅም። 4ኛ/ አንድን ነገር ደጋግመን እየሠራን የተለየለ ነገር የምንጠብቅ ቂሎች ሆነናል። 5ኛ/ ፍርሃት አደንዝዞናል። 6ኛ/ ከውድቀቶቻችን መማር አልቻልንም እና 7ኛ/ ለውጥን ወደ ግለሰብ ደረጃ በማውረድ ራሳችንን መቀየር አልቻልንም።

**ክቡራትና ክቡራን**

- ጥቂትም ቢሆኑ ያሉንን አስተዋዮቻችን ማራከስ ትተን አክብረን መስማት ከለመድን፤ ችግሮቻችንን በብልሃት ለመፍታት ጥረት ካደረግን፤
- ዳተኝነትን አስወግደን፤ በእርስ በርስ መናቆር ጊዜ ማጥፋታችንን ትተን የተግባር ሰዎች ከሆን፤
- አዳዲስ ስልቶችን ለመጠቀም ፈቃደኞችና ዝግጁዎች ከሆን፤
- ከፍርሃት ተላቀን ለነፃነታችን በጀግንነት መቆም ከቻልን፤
- ከውድቀቶቻቸን ትምህርት ወስደን ከወደቅንበት በፍጥነት ተነስተን በበለጠ ልበሙሉነት መንገዳችንን መቀጠል ከቻልን እና
- ለውጥን ወደ ራሳችን በማውረድ ኤጭ የነበርነው አሃን፤ አሃ የነበርነው ደግሞ ፈጣኑን ወይስ ፈታሹ ሆነን ከተገኘን ፍትህና እኩልነት የነገሰባት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ነፃ ዜጎች የምሆንበት ቀን ሩቅ አይሆንም።

**ስላዳመጣችኝ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ማርች 27 ቀን 2010 አስሎ፣ ኖርዌይ የቀረበ**

## ከኢትዮጵያ ተባረው የነበሩ ኤርትራዊያን ንብረቶች የሆኑ ቤቶች በወያኔ ካድሬዎች በህገ-ወጥ አራጣ ተሸጠው እንደነበር ታወቀ

በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት ከኢትዮጵያ ተባረው የነበሩ የኢትዮጵያ ወይም የኤርትራ ዜግነት የነበራቸው በርካታ ኤርትራውያን ንብረቶች በወያኔ ካድሬዎች በህገ-ወጥ አራጣ ተሸጠው እንደነበር የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ለማወቅ ችሏል።

በወቅቱ የኤርትራውያኑን ቤቶች ከወያኔ ካድሬዎች ህገ-ወጥ በሆነ አኳኋን ገዝተው የነበሩት ግለሰቦችም፣ በቅርቡ የወያኔው አገዛዝ ለፖለቲካ ፍጆታ ሲል ኤርትራውያን ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው ንብረቶቻቸውን እንዲወስዱ ጥሪ ማድረጉን ተከትሎ መጠበባቸውን ለማወቅ ተችሏል። ቤቶቹን የገዙበት ሁኔታ ህጋዊ ስላልሆነና ባለቤትነታቸውን የሚደግፍ ህጋዊ ዶኩመንት ባለመኖሩ፣ እራሳቸውን ከችግር ውስጥ ለማውጣት በሚል ቤቶቹን በርካሽ መሸጥ መጀመራቸውን ዘጋቢያችን ከተለያዩ ምንጮች ያገኛቸው መረጃዎች አስረድተዋል።

ዘረኛው እና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ስልጣን በጥቂት ምርጦች ቁጥጥር ስር ለማድረግ በቀረጸው ፖሊሲ አማካኝነት፤ ስልጣን ላይ በቆየባቸው ባለፉት ሃያ አመታት ዘርፈ-ብዙ ዘረፋዎችን ሲያካሂድ መቆየቱን የሚያሳዩ በርካታ ዘገባዎች ከዚህ ቀደም ማውጣታችን ይታወቃል።

## የግቤ ግድብ ግንባታን ይቃወማሉ ተብለው የሚገመቱ ዜጎች እስራትና እንግልት እየደረሰባቸው መሆኑ ታወቀ

የግቤ ግድብ ግንባታ በአካባቢው ነዋሪዎች እና የአካባቢ ጥበቃ ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል በሚል ተቃውሞ ሊያስነሱ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ ዜጎች እስራትና እንግልት እየደረሰባቸው መሆኑ ተዘገበ።

ኢንተርናሽናል ሪቨርስ የተባለ ድርጅት ቅዳሜ እለት በድረ-ገጹ ላይ ባወጣው ዘገባ፥ የግድቡን መገንባት የሚቃወሙ ቃላት ያሉበትን ካናቴራ ባለማወቅ የለበሰ ግለሰብ መታሰሩን ገልጿል። በግድቡ ግንባታ ላይ ጥናት ለማድረግ ለመጡ ተመራማሪዎች የአስተርጓሚነት አገልግሎት የሰጠ ኢትዮጵያዊ ዜጋም በአገር ክህደት ወንጀል ተከሶ መታሰሩም ተዘግቧል። ድረ-ገጹ በመጨመርም፥ የግቤ ግድብ ግንባታ ሁኔታና መጪው የምርጫ ተውኔት የሚመሳሰሉበት ነገር ቢኖር ሁለቱም በአፈና የተከበቡ መሆናቸው ነው በማለት መለስ ዜናዊና ግብረ አበሮቹ በዜጎች ላይ እያደረሱ ያሉትን ወከባና እንግልት አጋልጦአል።

## በካናዳ አገር ቶርንቶ ከተማ የሚገኙ . . . ከገጽ 1 የዞረ

ድርጅት እና የግንቦት 7 ንቅናቄ የቶሮንቶ ድጋፍ ሰጪ ቡድን፤ እንዲሁም በቶሮንቶ የኦሮሞ እና ኦጋዴን ኢትዮጵያውያን ማህበራት የተዘጋጀ እንደሆነ መግለጫው አሳይቷል። እነዚሁ ድርጅቶች እና ማህበራት ዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ በሰኔ ወር ወደ ካናዳ ለስብሰባ ሲመጣም ተመሳሳይ ሰልፍ ለማድረግ አላማ እንዳላቸው የታወቀ ሲሆን፤ ሌሎች የኢትዮጵያውያን ድርጅቶችም ለዚህ አላማ እንዲቀላቀሏቸው ጥሪ አቅርበዋል።

## ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ አሁንም . . . ከገጽ 1 የዞረ

የሲዳማ ዞን አርሶ አደር ለምን የወያኔ አባል እንደሆነ ሲገልጽ ፥ "እኔ የኢህአዴግ አባል ነኝ፤ ነገር ግን የምደግፈው ተቃዋሚዎችን ነው። የኢህአዴግ አባል መሆን ማለት ምንም ማለት አይደለም። እኔ አባል የሆንኩበት ምክንያት እርዳታ ለማግኘት ነው። እርዳታ ለማግኘት፥ ለፓርቲው መዋጮ የተከፈለበትን ደረሰኝ ማሳየት ያስፈልጋል። መዋጮ የምከፍለውም መጨቆን እና መዘንጋት ስለማልፈልግ ነው።" ማለቱን መዘገባችን ይታወሳል።

## አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ፤ ኢትዮጵያውያን . . . ከገጽ 1 የዞረ

በግለሰቦች ላይ ካተኮሩ አተካራዎች እራሳቸውን ነፃ በማድረግ፤ በህዝብ ትግል የተገኘውን የዲሞክራሲ ጭላንጭል ሙሉ በሙሉ አሟጦ የገደለውንና አገራችንን ለከፋ ችግር እንዲሁም የመበታተን አደጋ የዳረገውን የወያኔ አገዛዝ ለመጣል በሚደረገው ትግል ላይ መረባረብ ይኖርባቸዋል በማለት መክረዋል።

## በረከት ስምኦን፥ ለኦሮሞ ፌዴራሊስት ፓርቲ በመቀስቀሳቸው የተገደሉት አቶ ቢያንሳ ዳባ የገዢው ፓርቲ አባል ናቸው አለ

የኦሮሞ ፌዴራሊስት ኮንግረስ ፓርቲ አባል የሆኑት አቶ ቢያንሳ ዳባ መጋቢት 29 ቀን በወያኔ ካድሬዎች ድብደባ ደርሶባቸው ሆስፒታል ከገቡ በኋላ ሚያዝያ 8 ቀን ህይወታቸው ማለፉን ሬውተርስ የዜና አገልግሎትን በመጥቀስ መዘገባችን ይታወሳል።

የዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ባለስልጣን የሆነው በረከት ስምኦን ግን በግለሰቡ ላይ የተደረገ ድብደባ መኖሩን የካደ ሲሆን፤ ግለሰቡ የኦሮሞ ፌዴራሊስት ኮንግረስ ፓርቲ ሳይሆን የገዢው ፓርቲ አባል ናቸው ሲል አዣንስ ፍራንስ ፕሬስ ለተባለው የዜና አገልግሎት ቃሉን ሰጥቷል።

እንደ በረከት ስሞን አባባል ሟቹ አቶ ቢያንሳ ዳባ የወያኔ ፓርቲ አባል የነበሩ እንኳ ቢሆኑ፤ የግንቦት 7 ድምጽ ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ እንደገለጸው ህዝባችን ከወያኔና ካድሬዎቹ የሚደርስበትን አድልዎና ሰቆቃ ለመከላከል "ወይን ለመኖር" በሚል ስልት በግዴታ የሚጫንበትን የአባልነት ክፍያ ለወያኔ እየከፈለ፤ ለመብቱና ለሰብዓዊ ክብሩ ሲል ግን ነጻነት ያቀዳጁኛል ከሚላቸው ጸረ ወያኔ ሃይሎች ጋር መሰልፉን በገሃድ ማረጋገጥ መጀመሩን ያመላክታል ተብሎአል ። ወያኔ 4ሚሊዮን አባላት አሉኝ የሚለው በራሳቸውና በአገራቸው ላይ እየተፈጸመ ያለው ሰቆቃ እያንገበገባቸው ብሶታቸው ገንፍሎ ለመውጣት ቀን የሚጠባበቀውን እነደ አቶ ቢያንሳ ዳባ ያሉትን ዜጎች በጉያው አቅፎ እንደሆነ በረከት ከሰጠው ማስተባበያ መረዳት ይቻላል የሚሉ በርካቶች ናቸው።

## ኢትዮጵያን አሜሪካን ካውንስል የባራክ ኦባማ አስተዳደር በመጪው ግንቦት ወር በኢትዮጵያ ሊካሄድ የታቀደውን የምርጫ ተውኔት ውጤት እንዳይቀበል ጥሪ አደረገ

ድርጅቱ ቅዳሜ እለት ባወጣው መግለጫ የዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ አገዛዝ ከመጪው ወር ምርጫ ተብዬ በኋላ እራሱን አሸናፊ ብሎ እንደሚያውጅ ከወዲሁ የታወቀ እንደሆነና፤ ይህንንም እውን ለማድረግ አገዛዙ ከምርጫ 97 ማግስት ጀምሮ ሲሰናዳ መቆየቱን ገልጿል።

መግለጫው፥ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እንቅስቃሴ የሚገታው የመያዶች ህግ እና ጸረ-ሽብርተኝነት አዋጅ የሚባለው ህግ ከዚህ ዝግጅት ውስጥ የሚጠቀሱ መሆናቸውን ገልጾ፤ እንደዚህ በታፈነ የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ ሆኖ ነፃ ምርጫ የማይታሰብ ነው ብሷል።

## የወያኔን የምርጫ ግርግር የሚመለከቱ ቅኔ ብጤዎች

1. ተውሥሳክ ይዞን ኢንፍሉዌንዛ
እጅግ ተጎዳን እንደዋዛ፣
ሻከረ ጉሮሮአችን
እጅግ ታፍኖ ድምፃችን፨።

2. ደጋ ብንወጣ ተቆጡን
ቆላ ብንወርድ ገላመጡን፣
ይገኝ እንደሆነ እፎይታ
ለወደፊቱ ለዘለቄታ
ከመጣጣር የተሻለ
ከእንግዲህማ ምን ምርጫ አለ?

3. እስትንፋስ አጥሮኝ ደክሜ
እንዳልጣራ በምን አቅሜ፣
እንዴት ልግለጸው ስሜቴን
ወይ ድምጽ-አልባ መሆን!

*ሰውባገሩ ሆለችሣ*
*ሚያዝያ 20 ቀን 2002*


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ** እና **በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**
ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን g7radio@ginbot7.org **ወይም** በስልክ ቁጥር 0044- 203-286- 9661